#DEFYHATENOW

# ማንነት እና አውድ

# ግንዛቤ ስለ ቅደመ - ፍረጃ

በአለም ላይ ያሉ ማህበረሰቦች የተለያዩ ብሄሮች፣ ሃይማኖቶች ወይም የባህል ቡድኖች ካላቸው ሃገሮች የተዋቀሩ ሲሆኑ አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ቡድኖች የሚገባቸውን ቦታ ያለማግኘት ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። ይህም በታሪክ፣ በቅኝ ግዛት አሻራ ወይም በቅርብ ክስተቶች የተነሳ ሊሆን ይችላል። ይህም ወደ ውጥረት ያመራል፤ በመቀጠልም ግጭት ሊፈጥር ይችላል።

ማንነቶች የተወሳሰቡ ነገሮች ስለሆኑ በማንነት ላይ የተመሰረቱ ግጭቶችን ለመቆጣጠር በጣም ከባድ ነው። በማህበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው ቡድኖች ኢላማ ስለሆነው ማንነታችን ግንዛቤው አለን። ከተወሰነ ደረጃ በላይ ቅርበት ስለሌለን ሰዎች በቅድመ-ፍረጃ እንድንሞላ እና የተዛባ አመለካከት እንዲኖረን ተደርገናል።

**ማንነቶቻችን ቋሚ ነገሮች አይደሉም፤ በየቀኑ የምንደራደርባቸው ነገሮች ናቸው።**

## ስለቅድመ - ፍረጃ አጠቃላይ አስተሳሰቦች (Cotton, 1993)

- ቅድመ-ፍረጃ በልምምድ የሚመጣ ነገር ነው፤ በልምምድ ማቆምም ይቻላል።
- ቅድመ-ፍረጃን በሚመለከት ውጤታማ የሆነው ዘዴ እራስ ላይ ትኩረት ማድረግ እና ቀጥሎ ከቡድኖች ጋር ያለን ተመሳሳይነት እና ልዩነት መመርመር ነው።
- ስለራሳቸው ጥሩ ስሜት የሚሰማቸው ሰዎች ሌሎችን ዝቅ ማድረግ አያስፈልጋቸውም።
- መረጃዎች ብቻ ወደ ተሻለ የእርስ-በርስ ግንኙነት አይመሩም። ይህንን ለማድረግ የህብረት አስተምህሮ  እና በጥልቀት ማሰብ ላይ ያተኮረ ትምህርት ያስፈልጋል።

## ውጤታማ ለመሆን :

- የእርስ-በርስ መካከል የሚደረግ ውይይት ላይ እውነተኛ የሃሳብ ልውውጥ እንዲኖር ቦታ ሊሰጠው ይገባል፡፡
- በልዩነቶች እና በአለመግባባቶች ላይ ውይይት ማድረግ፡፡
- ውይይቱ “ከባህላዊ” መሪዎች ባለፈ ሁሉንም የማህበረሰብ ወኪል ወይም ተጠሪ የሚያካትት መሆን አለበት፣ በተለይም የሴቶች፣ የወጣቶች እና የተፈናቃዮች / አናሳ ማህበረሰቦችን ድምፅ ጎልቶ እንዲሰማ የሚያደርግ መሆን አለበት።